

**የእጩ ስም፦** Ry Armstrong (እነርሱ/የእነርሱ)

**የዘመቻ ስም፦** Armstrong for All

**የዘመቻ ድር ጣቢያ፦** [armstrongforall.com](armstrongforall.com)

**የከተማ ሥራ መደብ፦** Mayor of Seattle

**የዘመቻ ስልክ ቁጥር፦** +1 206-657-6287

በSeattle እምብርት ላይ፣ የቤተሰቤን አሻራዎች ተከትዬ እንደ ሰራተኛ አደራጅ ሆኜ እቆማለሁ። ከተግዳሮት በፍጹም አፈግፍጌ አላውቅም። ለሰራተኞች መብት፣ ተመጣጣኝ ለሆነ መኖሪያ ቤት እና ስነ ጥበባት ስታገል አመታትን ፈጅቻለሁ። እንደ Sustainable Seattle የጋራ ስራ አስፈጻሚ ዳይሬክተርነቴ፣ በመካከላችን ለሚገኙ በጣም ተጋላጭ የሆኑትን ሰዎች ለሚጠብቅ ንጹህ እና ፍትሃዊ ከተማ እሰራለሁ። ለአምስት አመታት ያህል ከሰራተኛ ማህበራት ጋር ሳደራጅ ቆይቻለሁ እና አሁን 50,000 ፈጣሪ ሰራተኞችን በመወከል ለፍትሃዊ ክፍያ፣ ደህንነት እና ጥቅማጥቅሞች ግፊት ለማድረግ AFL-CIO National Council of AEA ላይ በማገልገል ላይ እገኛለሁ። በSeattle LGBTQ Commission በነበረኝ ቆይታ እና የአመታት ተሟጋችነት የከተማ መንግስት እንዴት እንደሚሰራ አስተምሮኛል። ሰራተኛ ቤተሰቦች በከተማችን ውስጥ እንዲኳዙ ለመርዳት እና የአየር ንብረት ለውጥን ለመቀነስ የበካይ ጋዝ ልቀቶችን ለመቀነስ የሕዝብ መጓጓዣ የቀነሰ ወይም ነጻ ዋጋዎችን ማቅረብ አለበት ብዬ አምናለሁ። በመጀመሪያ 100 ቀናቶቼ 1,000 የመጠለያ አልጋዎችን ለመጨመር አቅጃለሁ። የመሬት አጠቃቀም ደንቦችን መቀየር የልጅ እንክብካቤ ማዕከላትን ለመገንባት እና Seattle የጠነከረ ለማድረግ ያግዘናል። በ2025 ወደኋላ አላፈገፍግም—ከተማችን ለተሻለ ነገ ለመፋለም ዝግጁ ናት። የእርስዎን ድጋፍ እጠይቃለሁ። ለሰዎች ቅድሚያ እንስጥ። አንድነት!

*ይህ እጩ በDemocracy Voucher Program ውስጥ በመሳተፍ ላይ ነው።*



**የእጩ ተወዳዳሪው ስም፥** ብሩስ ሃረል

**የምርጫ ዘመቻው ስም:** ብሩስ ለሲያትል

**የምርጫ ዘመቻው ድረ-ገጽ:** BruceforSeattle.com

**የስራ መደቡ:** የሲያትል ከንቲባ

**የዘመቻው ስልክ ቁጥር:** 206-569-8486

ከንቲባ ሆኜ ሳገለግልዎ ክብር ይሰማኛል! ቁርጠኛ ከሆኑ የከተማዪቱ ሰራተኞች በጋራ በመስራት፣ ሲያትል ደህንነቷ የተጠበቀ፣ ተመጣጣኝ ዋጋ ያላት፣ እና ሁሉንም የምትቀበል ለማድረግ እንሰራለን።

እስከ አሁን በሰራናቸው ስራዎች ኩራት ይሰማኛል:

በተመጣጣኝ ዋጋ የሚቀርብ መኖሪያ ቤት፣ የመኖሪያ ቤት ድጋፍ ተጋላጭ ለሆኑ ሰዎች ጨምሮ፣ እንዲሁም በሺዎች የሚቆጠሩ መኖሪያ ቤቶች ለሰርቶ ኣደሮች እና ቤተሰቦቻቸው የሚደረገውን የገንዘብ ድጋፍ ከፍ ማድረግ።

የሲያትልን ፖሊስ በሰው ሀይል ማጠናከርን ጨምሮ የህዝብን ደህንነት ማሻሻል፡ በህብረተ-ሰብ የሚደገፍ ግብረ-መልስ እና ተሳትፎ (CARE) ርህራሄን በማሳየት፣ ሲያስፈልግ በመሳሪያ ያልተደገፈ ምላሽን መስጠት፣ እንዲሁም በወጣቶች ደህንነት እና የጠብመንጃ ጥቃትን መከላከል ኢንቨስት ማድረግ።

ህንጻዎችን ንጹህ ለማድረግ አስቸኳይ የአየር ንብረት ርምጃ፣ ወደ ትራንዚት እና አስተማማኝ ወደ ሆኑት የእግረኛ መንገዶች ተደራሽነትን ማስፋት፣ የኤለክትሪክ መኪኖች ቻርጅ ማድረጊያ ማስፋት፣ እንዲሁም በሺዎች የሚቆጠሩ ኣዳዲስ ዛፎችን መትከል።

መሰረታዊ በሆኑ ኣገልግሎቶች ላይ ማተኮር– ጎዳናዎችን ማሻሻል፣ ፈቃድ ኣሰጣጥ ቀላል እንዲሆን ማድረግ፣ እና አነስተኛ ንግዶች ንቁ እንዲሆኑ መደገፍ።

ቫውቸሮችዎን እና ድምጾችዎን ተጠቅመን፣ ወደ ፊት መጓዛችንን እንቀጥላለን!

የመኖሪያ ቤቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ለማቅረብ ማስፋት– ለቤተሰብ ተስማሚ የሆኑ ቤቶች ለትምህርት ቤቶች ቅርብ የሆኑ ለትራንዚት ተደራሽ የሆኑ ኣፓርትሜንቶች እና ኮንዶሚኒየሞችን፣ ተደራሽነትን መጨመር አለብን፣ ዋጋን መቀነስ፣ እንዲሁም ለትውልድ የሚተላለፍ ሀብትን መፍጠር።

ደህንነትን ማሳደግ– የሲያትል ፖሊስ መምሪያ (SPD) ምልመላ፣ በህብረተ-ሰብ የሚደገፍ የግብረ-መልስ እና ተሳትፎ (CARE) ቡድንን ማስፋፋት፣ ብጥብጥን መቀነስ፣ ፈንታሊን እና ሌሎች ጎጂ ነገሮችን በመጠቀም ላይ ትኩረት መስጠት።

የሲያትልን መጪ ጊዜ ማፋጠን–ከዌስት ሲያትል እስከ ባላርድ ቀላል ባቡር፣ ዋተር ፍሮንትን ማጠናቀቅ እንዲሁም ሲያትል ሴንተርን እንደገና ማሰብ፣ ዳውንታውንን እንደ ታላቅ የኤመራልድ ከተማ ወደ ነበረችበት መመለስ።

ቀጣይ የሆነ ድጋፋችሁ እንዳይለየኝ እጠይቃለሁ

*ይህ እጩ በዲሞክራሲ ቫውቸር ፕሮግራም ውስጥ እየተሳተፈ ነው።*



የእጩ ስም፡- Joe Mallahan

የዘመቻ ስም፡- Mallahan ለከንቲባ

የዘመቻ ድር ጣቢያ፡- joemallahanforseattlemayor.com

የከተማ ሥራ መደብ፡- የሲያትል ከንቲባ (Mayor of Seattle)

የዘመቻ ስልክ ቁጥር፡- 206.229.8149

ለከንቲባ እሮጣለሁ ምክንያቱም ሲያትል ከሀሳቦቹ ጋር ተስማምቶ መኖር ይችላል ብዬ ስለማምን ነው። የSeattle ከተማ አስተዳደር በተቀላጠፈ ሁኔታ የሚሰራ ከሆነ፣ ከተማዋ እንደ ሀገር አቀፍ ተራማጅ አመራር ምሳሌ ሆና ከ MAGA እንቅስቃሴ ጋር ከተያያዘው ስርዓት አልበኝነት እና ጭካኔ በተቃራኒ ልትቆም ትችላለች።

ከንቲባ እንደመሆኔ መጠን፣ ከተማዋ የሁሉንም ሰው ፍላጎት በፍትሃዊነት እና በብቃት እንድታገለግል አረጋግጣለሁ። በእውነተኛ የፖሊስ ቁጥጥር እና የማህበረሰብ እምነትን እንደገና መገንባት — የህዝብን ደህንነት በከፍተኛ ሁኔታ ማሻሻል አለብን። በመንገዶቻችን ላይ በትክክል እየተከሰተ ባለው ነገር ላይ ለመቆም በመጀመሪያው አመት 50 የጥበቃ ጉዞዎችን አጠናቅቄያለሁ።

ቀይ መስመርን እቆርጣለሁ፣ የቤቶች ምርትን አፋጥኛለሁ፣ እና የሚሰሩ ቤተሰቦችን በሚያገለግሉ ፕሮጀክቶች ላይ ወጪ አደርጋለሁ። በተመጣጣኝ ዋጋ ቤቶችን ለመገንባት፣ የአዕምሮ ጤና እና የሱስ ህክምና ተደራሽነትን ለማስፋት እና 5,000 የአደጋ ጊዜ አልጋዎችን ለማድረስ የፌዴራል የግብር ብድር እጠቀማለሁ በመጀመሪያው አመት - ሰዎች በጎዳና ላይ በሚኖሩበት ጊዜ ሱስን ማከም አይችሉም።

ከግንባር መስመር ሰራተኞች ጋር ትከሻ ከ ትከሻ በመስራት መካከለኛ መጠን ያላቸውን ንግዶችን በመዞር ስራዬን በሙሉ የለውጥ ወኪል ሆኛለሁ። በT-Mobile የደንበኞች አገልግሎት ተወካዮችን አዳምጣለሁ እና የብድር አቅርቦትን እና ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው በሚሊዮኖች ለሚቆጠሩ ቤተሰቦች ዝቅተኛ ዋጋ ሰጥቻለሁ። እንደ ማህበረሰብ አደራጅ፣ ትልልቅ የከተማ ችግሮችን ለመፍታት ሰዎችን ሰብስቤ ነበር።

Seattle ደህንነቱ የተጠበቀ እና ተመጣጣኝ የመኖሪያ ቦታ ሆኖ መቆየቱን በማረጋገጥ ቤት እጦትን በጥንቃቄ መፍታት እንችላለን።

*እኚህ እጩ በዴሞክራሲ ቫውቸር ፕሮግራም ውስጥ እየተሳተፉ ነው።*



**የእጩ ስም፦** ጆ ሞሎይ (Joe Molloy)

**የዘመቻ ስም፦** ጆ ሞሎይ ለከንቲባ

**የዘመቻ ድር ጣቢያ፦** joemolloyformayor.com

**የከተማ ሥራ መደብ፦** የሲያትል ከንቲባ (Mayor of Seattle)

**የዘመቻ ስልክ ቁጥር፦** 206-590-1126

ጆ ሞሎይ እባላለሁ፤ የተመጣጣኝ የመኖሪያ ቤት አቅርቦት እና የአካል ጉዳተኞች መብት ተሟጋች ስሆን፣ የአሠራር ሥርዓቶችን በአዲስ እና በተሻለ መልኩ የሚያስብ ባለራዕይ እና በሰባራ የአሠራር ሥርዓቶች ግንባር ቀደም ተጠቂ ካደረጉኝ ተሞክሮዎች የሕይወት ቀስሞ የተቀረጸ ጠንካራ መሪ ነኝ።

እኔ በሙያዬ ፖለቲከኛ ሳልሆን ለችግሮቻችን አሁኑኑ መፍትሔ ማበጀት አለብን የሚል ጥልቅ እና ጠንካራ ስሜት የሚመራኝ የሕዝብ አገልጋይ ነኝ። በዚህ ምርጫ የተሳተፍኩት በከተማችን ያለውን የቤት አልባነት እና የቤት እጥረት ችግር ለመፍታት ብሎም እስከ ወዲያኛው ለመቅረፍ ነው።

ሀሳቤን ሙሉ በሙሉ መግለጽ ከምችልባቸው ጥቂት ቦታዎች አንዱ እንደሆነ በማመን ነበር ሆን ብዬ ወደ ሲያትል የመጣሁት። ሌሎች ብዙዎችም በዚሁ ምክንያት ይህንን ከተማ ቤቴ ብለው እንደሚጠሩት አውቃለሁ። ሆኖም ግን አሁን ያሉት የአሠራር ሥርዓቶቻችን እሴቶታችንን እንደማይወክሉ ሁላችንም እናውቃለን።

ፈቃደኛ ሆነን በቁርጠኝነት ከተነሳን ግን አሠራሮቻችን እሴቶቻችንን እንዲወክሉ ማድረግ እንችላለን።

የምርጫ ዘመቻችን የቤት አልባነት እና እጥረት ችግሮችን ስለመቅረፍ ብቻ ሳይሆን፣ አካታች እና ሁሉን አቀፍ የማኅበራዊ እና የመንግሥት አገልግሎቶችን በከተማዋ በመገንባት ሰዎችን ቤት አልባ ሊያደርጉ የሚችሉ ኢጋጣሚዎች እንዳይኖሩ ስለማድረግ ነው። በዚህ ረገድ ፈር ቀዳጅ ከተማ መሆን እንደምንችል አምናለሁ። ይህ ደግሞ ለሌሎች ከተማዎች አርዓያ ያደርገናል።

የቤት አልባነት እና እጥረት ችግርን ከቀረፍን፣ እየቀረፍን ያለነው አንድ ትልቅ ችግርን ብቻ ሳይሆን ወደፊታችን አስተማማኝ፣ ዘላቂ እና በመልካም አጋጣሚዎች የተሞላ እንዲሆን የሚያደርግ መሠረት እየጣልን ነው።

በዚህ ምርጫ ላይ የተሳተፍኩትም ይህንኑ ለማድረግ ሲሆን፣ ድጋፋችሁንም የምጠይቀው ለዚሁ ነው።

*እኚህ እጩ የዴሞክራሲ ቫውቸር ፕሮግራም ተሳታፊ ናቸው።*



**የእጩ ስም፦** Katie Wilson

**የዘመቻ ስም፦** ዊልሰን ለሲያትል

**የዘመቻ ድር ገጽ፦** wilsonforseattle.com

**የከተማ ሥራ መደብ፦**የሲያትል ከንቲባ

**የዘመቻ ስልክ ቁጥር፦** 607- 301 - 1836

ስሜ Katie Wilson ይባላል እና የሲያትል ቀጣይ ከንቲባ ለመሆን እየተወዳደርኩ ነው።

የሙያዬን ያለፉት 14 አመታት ለሰራተኛ ቤተሰቦች ዋና ዋና ድሎችን ለማቀናጀት የተለያዩ ጥምረትዎችን በመገንባት እና በመምራት አሳልፌአለሁ፦ ከፍ ያለ ዝቅተኛ ደመወዝ፣ ጠንካራ የተከራይ ጥበቃ፣ የበለጠ ተመጣጣኝ መኖሪያ ቤት፣ የተሻለ የህዝብ መጓጓዣ እና አስቀድሞም ከአቅም በላይ ከምንከፍለው ከኛ ይልቅ ግብር ለመክፈል አቅሙ ያላቸውን ማስከፈል። ታላላቅ ነገሮችን ለማሳካት በየተለያዩ አይነት ሰዎችን እንዴት ማሰባሰብ እንደምችል አውቅበታለው።

የአሁኑ ከንቲባ ከ2008 ጀምሮ በከተማ ማዘጋጃ ቤት (City Hall) ውስጥ ፖለቲከኛ ነበሩ። በዚያ ጊዜ ውስጥ፣ በሲያትል ቤት ለመከራየት ወይም ለመግዛት የሚወጣው ወጪ ከእጥፍ በላይ ጨምሯል፣ እና ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ብዙ ሰዎች በጎዳናዎቻችን ላይ መጠለያ ያጡ ሆነዋል።

እንደዚ መሆን የለበትም። ለሁላችንም ቤት መገንባት እንችላለን። ንቁ እና ለኑሮ ምቹ የሆኑ ሰፈሮች ሊኖረን ይችላል። የሚበለጽጉ ትናንሽ ንግዶች ሊኖረን ይችላል። ደህንነታቸው የተጠበቀ በመሆናቸው ደህንነት የሚሰማባቸው መንገዶች ሊኖረን ይችላል። የስደተኞች ማህበረሰቦችን መጠበቅ እና ለሁሉም እድል መፍጠር እንችላለን። ይህንን አንድ ላይ ማድረግ እንችላለን። ሲያትል ግን አዲስ አመራር ያስፈልጋታል።

ይህ የእርስዎ ከተማ ነው። ኃይልዎን እና ድምጽዎን ወደ ከተማ ማዘጋጃ ቤት City Hall ማምጣት እፈልጋለሁ። አንድላይ ሆነን እናሳካው።

*እኚህ እጩ በዴሞክራሲ ቫውቸር ፕሮግራም ውስጥ እየተሳተፉ ነው።*



**የምርጫ እጩ ስም:-** ኢሳይያስ ዊሎግቢ (Isaiah Willoughby)

**የምርጫ ዘመቻ ስም:-** የህዝቡ ድምፅ

**የምርጫ ዘመቻ ድህረ ገጽ:-**

**የምርጫ ወንበሩ መደብ:-** የሲያትል ከንቲባ

**የምርጫ ዘመቻ ስልክ ቁጥር:-** (206) 228-4802

ሰላም፣ ሲያትል። ስሜ ኢሳይያስ ዊሎግቢ እባላለሁ፣ እኔ የእርስዎ ቀጣዩ ከንቲባ ለመሆን እየተወዳደርሁ ነው።

እኔ የፖለቲካ ሙያተኛ አይደለሁም— እኔ ከተማችንን እየተጋፈጠ ያለውን ትክክለኛ ተግዳሮቶች የሚገባኝ አንድ የማህበረሰብ አባል ነኝ። በመኖሪያ ቤቶች ውስጥ ሰርቻለሁ፣ ሥርዓቱን አጥንቻለሁ፣ እየጨመሩ በመጡ ዋጋዎች እና ብልሹ ፖሊሲዎችን በመታገል ውስጥ ኖሬአለሁ።

ከሰሜን ሲያትል ኮሌጅ በቤትና ንብረት አሻሻጭነት (Real Estate) ዲግሪ አግኝቻለሁ እና በንግድ ስራ ፈጠራ እና ማህበረሰብ በማደራጀት ልምድ አለኝ። ችግሮቹን ስላጋጠሙኝ አውቃቸዋለሁ—እናም እውነተኛ መፍትሄዎች የሚመነጩት በቀጥታ ተጽእኖ የደረሰባቸውን ሰዎች በማዳመጥ እንደሆነ አውቃለሁ።

እንደ ከንቲባ፣ እኔ ትኩረት የማደርገው በሚከተሉት ላይ ነው:-

- በእውነት የዋጋ ተመጣጣኝነት ያለው መኖሪያ ቤት
- ከህብረተሰቡ ጋር መተማመንን የሚገነባ የህዝብ ደህንነት
- የሚሰሩ ቤተሰቦች እና አነስተኛ የንግድ ሥራዎች እንዲበለፅጉ የሚረዳ አንድ ጠንካራ የአካባቢ ኢኮኖሚ

ይህ ዘመቻ "የሕዝቡ ድምፅ" ተብሎ የተጠራው ምክንያቱ እኔ አመራር በሩ ክፍት፣ ግልጽነት ያለው፣ እና በአገልግሎት ላይ የተመሰረተ—እንጂ እንደተለመደው ፖለቲካ እንደ ወትሮው መሆን የለበትም ብዬ ስለማምን ነው።

በጋራ አንድ ላይ፣ እኛ እያንዳንዱ የሚሰማበት፣ የሚደገፍበት፣ እና የሚበረታታበት/ ሃይል የሚሰጠው ሲያትል መገንባት እንችላለን።

ስለ እርስዎ እምነት እና ድምጽ አመሰግናለሁ።

*እኚህ እጩ በዴሞክራሲ ቫውቸር ፕሮግራም ውስጥ እየተሳተፉ ነው።*



**የእጩ ስም:-** Ann Davison

**የዘመቻ ስም:-** ጎረቤቶች ለAnn

**የዘመቻ ድረገጽ:-** https://neighborsforann.com/

**የከተማ ሥራ መደብ:-** ለከተማ ጠበቃ እጩ

**የዘመቻ ስልክ ቁጥር:-** (206) 257 - 2206

ከ 2022 ጀምሮ የሲያትል ከተማ ጠበቃ ሆኜ ማገልገል ትልቅ ክብር እና በሲያትል የህዝብን ደህንነትን ለማሻሻል ላይ በማተኮር እንድቀጥል ጉልበት ይሰጠኛል። የጥቃቅን ወንጀሎችን የፍትህ ስርዓታችንን በእውነተኛ ጊዜ ተጠያቂነት ላይ የማተኮር፣ ህጎችን ወይም የመንግስታችንን አሰራር ለማሻሻል ከህግ አውጪዎች ወይም ከከተማ ምክር ቤት ጋር መስራት፣ ስርዓታችን ለህዝብ በተሻለ ሁኔታ እንዴት መስራት እንደሚችል ላይ ትኩረት አድርጊያለሁ። የአደገኛ ዕፅ ወይም የሴተኛ አዳሪነት አካባቢዎችን በመከልከል የከተማችንን የህዝብ ቦታዎች ለመጠበቅ የሚያስችል ህግ አውጥቻለሁ፤ ለአደጋ የተጋለጡ ሰዎችን የሚበዘብዙ የወንጀል ድርጅቶችን በማከሸፍ ላይ እሰራለሁ። ህዝቡ ስለ ስራዬ እና የውሳኔዎቼ መሰረት እንዲያውቅልኝ ከዚህ በፊት ታይቶ በማይታወቅ የመረጃ ግልጽነት እና የማህበረሰብ ተደራሽነት በሆነ አቃቤ ህግ መስሪያ ቤት ግንባር ቀደም ነኝ። የህዝብን ደህንነት ለማረጋገጥ በሚል አላማ፣ ለመስረቅ እጅግ በጣም ቀላል የሆኑ ርካሽ መኪኖቻቸውን ወደ ገበያዎቻችን የሚያስገቡ የመኪና አምራቾችን ከስሻለሁ። ከኬሚካል አምራች ግዙፍ ኩባንያ ጋር ባደረግኩት ክስ በሀገሪቱ ታይቶ የማይታወቅ የከተማ ስምምነት በማድረግ 160 ሚሊዮን ዶላር ለዱዋሚሽ የአካባቢ ጽዳት ስራ ወደ ሲያትል እንዲገባ አድርጊያለሁ። ሲያትልን እና ህጎቿን ለመጠበቅ እዚህ ተገኝቻለሁ፤ ዳግም ብመረጥ በምንም መልኩ ሳልታክት ወይም ሳላቋርጥ እሰራለሁ።

*ይህቺ እጩ በዲሞክራሲ ቫውቸር ፕሮግራም ውስጥ እየተሳተፈ ነው።*



**ለምርጫ የእጩ ስም:-** ኤሪካ ኢቫንስ (Erika Evans)

**የምርጫ ዘመቻ ስም:-** ኤሪካ ኢቫንስን ምረጡ

**የምርጫ ዘመቻ ድህረ ገጽ ጣቢያ:-**

www.ElectErikaEvans.com

**የከተማ የምርጫ ወንበር:-** የከተማ ጠበቃ/ የከተማ አቃቤ ሕግ

**የምርጫ ዘመቻ ኢሜይል:-** info@ElectErikaEvans.com

እኔ ለቀጣዩ የሲያትል ከተማ ጠበቃ ለመሆን እየተወዳደርኩ ነኝ ምክንያቱም ይህችን ከተማ እወዳታለሁ — እና እኛ የተሻለ መስራት እንደምንችል አውቃለሁ። እኔ የተወለድኩት በሲቪል እና በኢኮኖሚያዊ መብቶች በተሞላ ቤተሰብ ውስጥ ነው፣ እና እኔ አብዛኛው ማህበረሰቦቻችን ያጋጠሟቸውን ትግሎች ኖሬአለሁ። እኔ ሙያዬን ያሳለፍኩት ለመብታችን በመከላከል እና ሰዎች ደህንነታቸው የበለጠ የተጠበቀ እንዲሆን ህጎችን በመቅረጽ ነው።

በሲያትል ከተማ አቃቤ ህግ ጽህፈት ቤት በሁለቱም የወንጀል እና የፍትሐ ብሔር ክፍሎች ውስጥ የሰራሁት እጩ እኔ ብቻ ነኝ። እኔ ይህ ቢሮ እንዴት እንደሚሰራ — እና እውነተኛ ለውጥ እንዴት እንደሚቀርብ አውቃለሁ። እንደ ጊዜያዊ የማዘጋጃ ቤት ፍርድ ቤት ዳኛ፣ እኔ ተጠያቂነት ምን እንደሚመስል አይቻለሁ። እንደ አንድ የፌደራል አቃቤ ህግ፣ እኔ ደሞዝ የሚሰርቁትን ሠራተኞች ከስሼአቸዋለሁ፣ የጥላቻ ወንጀሎችን ለፍርድ አቅርቤ አለሁ፣ ሽጉጥ እና ፈንታኒል አዘዋዋሪዎችን ተጠያቂ አድርጌአቸዋለሁ እና ለጥቃት ሰለባ ለሆኑ ተጐጂዎች ቆሜላቸዋለሁ።

እውነተኛ ደህንነት ማለት ከመታሰር በጣም የበለጠ ነው። ማለትም ተጠያቂነት ከርኅራኄ ጋር፣ ጠንካራ የጉልበት ሥራና የተፈጥሮ አካባቢ ጥበቃዎች፣ የእንደገና መራቢያ ነፃነት እና ከእስር ቤት ሌላ እውነተኛ አማራጮች ማቅረብ ማለት ነው። ለዚያም ነው እኔ አዲስ የማህበረሰብ ፍርድ ቤት በመልሶ ማቋቋም ላይ ያተኮረ እንዲሆን የምሟገተው — በተዘዋዋሪ በሮች ላይ አይደለም።

በትራምፕ (Trump) አስተዳደር መብታችን እየተጠቃ ባለበት በዚህ ወቅት፣ እኛ ለመመከት በበቂ ልምድ፣ የጀርባ አጥንት እና መልሶ ለማጥቃት እውቀት ያለው የከተማው አቃቤ ሕግ የሚያስፈልገን። እኔ ዝግጁ ነኝ።

*እኚህ እጩ በዴሞክራሲ ቫውቸር ፕሮግራም ውስጥ እየተሳተፉ ነው።*



**የእጩ ስም፡-** Rory O’Sullivan

**የዘመቻ ስም፡-** Friends of Rory O’Sullivan

**የዘመቻ ድረገጽ፡-** www.electrory.com

**የከተማ የሥራ ኃላፊነት፡-** የከተማ ዓቃቤ ሕግ

**የዘመቻ ስልክ ቁጥር፡-** 206-356-9852

Seattle ከተማችንን ከአደጋ የተጠበቀ ለማድረግ ቅድሚያ የሚሰጠው የከተማ ዓቃቤ ሕግ ይገባዋል። ሁላችንም ፀረ-ወንጀል ነን፣ ነገር ግን ፀረ-ወንጀል መሆን ብቻውን በቂ አይደለም። አሁንም መፍትሄዎችን በመጠበቅ ላይ እንገኛለን።

የከተማው ዓቃቤ ህግ ቢሮ የማህበረሰብ ፍርድ ቤትን ዘግቷል፣ ከተመረጡት ዳኞች ጋር መጣላት መርጧል፣ ጠጥቶ ማሽከርከርን እስከ 85 ቀናት ድረስ የሚለወጥ ክስ እንዲመሰረት ፈቅዷል፣ ከህገ መንግስቱ ጋር በተቃረበ የስራ አስፈፃሚ ትዕዛዞች ላይም ምንም አላደረገም፣ እና ለመፍጠር ቃል የገቡትን አስተማማኝ እና የበለጠ መተዛዘን ያለበት ከተማ መፍጠር አልቻለም።

ለሰራተኞች በመታገል፣ የህግ ስርዓታችንን ፍትሃዊ ተደራሽነት በማረጋገጥ እና ንቁ ተባባሪ በመሆን የሥራ ዘመኔን በሙሉ አሳልፌያለሁ። በሲያትል ላይ ላሉ ችግሮች መፍትሄዎችን የሚያመነጭ የከተማ አቃቤ ህግ ቢሮን ለመምራት ተዘጋጅቻለሁ።

ከወንጀል አዙሪት ለማምለጥ እድል ለመስጠት የማህበረሰብ ፍርድ ቤትን ከተሻሻለ ክትትል ጋር እመልሳለሁ፣ ዳግም ወንጀሎች እስኪፈጸሙ መጠበቅን ለማስቆም ሲባል የቤት ውስጥ ጥቃት እና ጠጥቶ ማሽከርከርን ክሶች አፋጥናለሁ፣ ሰራተኞችን በስራ ቦታ ከሚኖር መጥፎ አያያዝ ለመጠበቅ ጠንካራ የስራ መስፈርቶችን ተግባራዊ አደርጋለሁ፣ እና ብቃት ያለው የከተማ ዓቃቤ ሕግ ቢሮ ለመፍጠር - በጥሩ አስተዳደር ላይ አተኩራለሁ።

ድጋፍ ሰጪዎች፡- የኢንሹራንስ ኮሚሽነር Patty Kuderer፣ የግዛቱ ሴናተር Rebecca Saldaña፣ የግዛቱ ተወካዮች Rebecca Saldaña እና Sharon Tomiko Santos፣ የቀድሞ የከተማው ምክር ቤት አባላት Tammy Morales እና Mike O’Brien፣ የSeattle አስተላላፊዎች ማህበር እና ሌሎችም።

*እኚህ እጩ በዲሞክራሲ ቫውቸር ፕሮግራም ውስጥ እየተሳተፉ ነው።*



**የእጩ ስም፦** ኔታን ሮስ

**የምርጫ ዘመቻ ስም፦** ለሮስ ድምፅ ይስጡ

**የዘመቻ ድር ጣቢያ፦** www.voterouse.com

**የከተማ የሥራ ኃላፊነት፦** የከተማ ጠበቃ

**የዘመቻ ስልክ ቁጥር፦** 206-593-2203

እኔ **ኔታን ሮስ** ነኝ፣ **የሕዝብ ጠበቃ፣ የሕግ ተሟጋች እና አባት**፣ ለሚቀጥለው የሲያትል **የከተማ ጠበቃ** ለመሆን በምርጫ እወዳደራለሁ። እኔ የሕዝብ ተከላካይ ጠበቃ ሙያዬን የተበላሹ ሥርዓቶች ሰባብረው በጣሉት፣ ለተጠያቂነት እና ሁለተኛ ዕድሎች እንዲያገኙ ለተደረጉ ሰዎች በመታገል ላይ ቆይቻለሁ።

እኔ በምርጫ የምወዳደረው ለዚህች ከተማ በጥልቅ ስለማስብ እና ለሁሉም **አቅም ላለው ብቻ ሳይሆን—ለእያንዳንዱ ሰው** የሚጠቅም የፍትህ ሥርዓት እንደሚያስፈልገን ስለማምን ነው። ትርጉም ያለው እንደገና ተሀድሶ እና ድጋፍ በማቅረብ እና ወደ እኛ ማህበረሰብ እንደገና ለሚቀላቀሉ ሰዎች እጅግ አሳሳቢ ከባድ ወንጀሎች ላይ እርምጃ በመውሰድ **እውነተኛ የሕዝብ ደህንነት መፍትሄዎች** ያስፈልጉናል። እኛ **የሠራተኞች እና ተከራዮችን ደህንነት መጠበቅ፣ ለወንጀል ተጎጂዎች ከዚህ የበለጠ ጠንካራ ማካካሻ በድጋፍ ገንዘብ ማቋቋም** እና **ለሲያትል በሂደት ላይ ያሉ እሴቶች** ማቋቋም ያስፈልገናል—በተለይ ከትራምፕ አስተዳደር ተከታታይ ጥቃት ለሚደርስባቸው። ለእኛ ያስባሉ ብለን በሪፐብሊካን የከተማ ጠበቃ መተማመን አንችልም።

እኛ አሁን ያለንበት የፍትህ አካሄዳችን እንዴት እንሠራ እንዳልሆነ እኔ በቅድሚያ እያየሁ ነው። ከእስር ቤት ሲወጡ እንደገና ወንጀል እንዳይሰሩ እኛ ብዙ ጊዜ፣ ሰዎች የወንጀል መንስኤዎችን አንስተን ሳናስተካክል ወይም አጥፊዎችን ሲወጡ ለስኬታማነት ሳናዘጋጃቸው በሥርአቱ ውስጥ ሰዎችን እናመላልሳለን። እኔ ትርጉም ያለው ተጠያቂነትን በማረጋገጥ የሕዝቡን ደህንነት በእውነት የሚያሻሽሉ **ውሂብ/በመረጃ-የተደገፉ ፖሊሲዎች** ላይ አተኩራለሁ።

እኔ **ይበልጥ ደህንነቱ የተጠበቀ፣ ይበልጥ ፍትሃዊ ሲያትል** ለመገንባት በምርጫ እየተወዳደርኩ ነው—እና እርስዎም አብረውኝ እንደሚቀላቀሉ ተስፋ አደርጋለሁ።

*እኚህ እጩ ተወዳዳሪ በዲሞክራሲ ቫውቸር ፕሮግራም ውስጥ እየተሳተፉ ነው።*



**የእጩ ስም:-** ኤዲ ሊን

**የዘመቻ ስም:-** ኤዲ ለሲያትል

**የዘመቻ ድር ጣቢያ:-** https://www.linforseattle.com/

**በከተማው የሚወዳደረው:-** በከተማው ምክር ቤት የስራ መደብ 2

**የዘመቻ ስልክ ቁጥር:-** 206-734-7412

ለቤቶች ቢሮ ረዳት የከተማ ጠበቃ እንደመሆኑ መጠን፣ ኤዲ በሺዎች የሚቆጠሩ ተመጣጣኝ መኖሪያ ቤቶችን በፈንድ ለመደገፍ ለዓመታት ሲሰራ ቆይቷል። በጣም እየጨመረ የሚሄደውን የኪራይ ዋጋ መቀነስ ቀዳሚ ተግባር መሆን አለበት ብሎ ያምናል። ኢዲ ከተማችንን በተለይ ደቡብ ዞን ለአስርት አመታት ሲከብድ የነበረውን አግላይ አከላለልን፣ መድልዎን፣ እና የስርዓታዊ የኢንቨስትመንት እጦትን፣ ለመፍታት ያለመታከት ይሰራል።

ኤዲ የታይዋናዊ ስደተኛ ልጅ ነው እና በሰሜን ካሮላይና እያደገ እያለ መድልዎ ገጥሞታል። የኮሌጅ ክፍያዎችን ለመክፈል በስኮላርሺፕ፣ በፋይናንሲያዊ እርዳታ እና በርካታ ስራዎችን በመስራት ይተማመን ነበር። እሱ የቤት ቀለም ቀቢ፣ በአካባቢው ቤተ ክርስቲያን የጽዳት ሠራተኛ፣ እና የብስክሌት መልእክተኛ ነበር። እንግዳው እንዳስቀመጠው፡ “የሲያትል አቅምን ያላገናዘበ የኑሮ ውድነት አስቸጋሪነት ለኤዲ አዲስ አይደለም፣እሱ ኖሯል።”

ኤዲ እየተወዳደረ ያለው የሲያትል ከባድ ፈተናዎችን ለመቅረፍ የሚደረገው ጥረት አጣዳፊ አለመሆኑ ስለተበሳጨ ነው። የህዝብ ደህንነት፣ አቅምን ያላገናዘበ የኑሮ ሁኔታ፣ የቤት እጦት፣ ወይም የተለያዩ ችግሮች ያሉባቸው የህዝብ ትምህርት ቤቶች፣ እሱ እርምጃ ለመውሰድ እና ተጨባጭ እድገት ለማድረግ ዝግጁ ነው።

ኤዲ ሲያትል የሁሉም ሰው ቦታ መሆን አለበት ብሎ ያምናል - እና ለዚያም ነው የምንመካባቸው አስፈላጊ አገልግሎቶችን ፈንድ ለማድረግ በሀብታም ኮርፖሬሽኖች እና እጅግ ባለጸጋዎች ላይ ግብር መጣልን ይደግፋል።

*ይህ እጩ በዲሞክራሲ ቫውቸር ፕሮግራም ውስጥ እየተሳተፈ ነው።*



**የእጩ ስም፡-** አዶኒስ ዳክስዎርዝ

**የዘመቻ ስም፡-**አዶኒስ ለሲያትል

**የዘመቻ ድር ጣቢያ፡-** AdonisForSeattle.com

**የከተማው አቀማመጥ፡-** የከተማው ምክር ቤት የስራ መደብ 2

**የዘመቻ ስልክ ቁጥር፡-** 206-495-5597

ያደግኩት በነጠላ እናት በቢኮን ሂል ላይ ባለ ትሪፕሌክስ ውስጥ ነው። በየአካባቢው ከጓደኞቼ ጋር ስጫወት አስደሳች ትዝታዎች አሉኝ። በትምህርት ቤቶች እና በአገልግሎቶች አቅራቢያ የሚገኝ መኖሪያ ቤት ለኛ መረጋጋት ወሳኝ ነበር።

ዛሬ፣ ሰዎች ስለ ሽጉጥ ጥቃት፣ ቤት መግዛት ባለመቻላቸው፣ ከቤታቸው ዋጋ ስለተጣለባቸው እና ለልጆች እድሎች እጦት ይጨነቃሉ።

ላለፉት 10 ዓመታት፣ በሲያትል ከተማ ውስጥ እንደ ተደራሽነት፣ ተሳትፎ እና የፖሊሲ ባለሙያ ሆኜ ሠርቻለሁ። በከተማው ውስጥ ሁሉ ነገሮችን ለማከናወን ሰዎችን በአንድ ላይ የማሰባሰብ ታሪክ አለኝ።

ለህብረተሰባችን የተሻለ መስራት እንደምንችል ስለማውቅ ነው የምሮጠው።

በአንተ ድምጽ፣ የሚገባንን ውጤት አገኛለሁ፡-

- በ Southend ውስጥ መኖር ለሚፈልጉ ሰዎች የተሻሉ የመኖሪያ አማራጮች; በቤታቸው እና በአካባቢያቸው ለመቆየት ለሚፈልጉ ሰዎች ተጨማሪ አማራጮች።
- የበለጠ ተጠያቂ የፖሊስ መኮንኖች፣ የኬር ቡድን ምላሽ ሰጪዎችን ማስፋፋት እና የሽጉጥ ጥቃትን የሚቀንሱ እና ህፃናትን እና ትናንሽ ንግዶችን የሚከላከሉ ጣልቃገብነቶች ላይ ኢንቨስት ማድረግ።
- የትራንስፖርት ቀረጥ ስኬትን በመገንባት በሬኒየር እና ኤም.ኤል.ኬ ላይ መኪኖችን ለማዘግየት፣ መጓጓዣን ደህንነቱ የተጠበቀ እና አስተማማኝ ለማድረግ እና ለሁሉም ተጠቃሚዎች ደህንነቱ የተጠበቀ፣ የበለጠ ሊገመቱ የሚችሉ እና ቀልጣፋ አማራጮችን ለማቅረብ እሰራለሁ።

*ይህ እጩ በዲሞክራሲ ቫውቸር ፕሮግራም ውስጥ እየተሳተፈ ነው።*



የእጩ ስም:- ጂኒ ቻን (Jeanie Chunn)

የዘመቻ ስም:- ለጂኒ ድምጽ ይስጡ

የዘመቻ ድር ጣቢያ:- votejeanie.com

የከተማ የምርጫ ወንበር:- የከተማው ምክር ቤት ምርጫ ወንበር 2

የዘመቻ ስልክ ቁጥር:- 206-255-4562

በዚህ ወሳኝ ወቅት ውስጥ፣ የሲያትል የምክር ቤት በእውነት የሚያዳምጥ አባል ያስፈልጋታል - አንድ በማህበረሰቡ ውስጥ ስር ያለው፣ በልዩ ፍላጎቶች ሁኔታ ውስጥ ያደገ፣ ለተራማጅ ለውጥ ለመታገል ዝግጁ የሆነ ሰው ያስፈልጋታል። እኔ ያንን ድምጽ ለመሆን እየተወዳደርኩ ነው።

ከተማችን ከባድ ተግዳሮቶች ተጋርጠውባታል:- ባለጠጎችን የሚጠቅሙ ወደኋላ ዘቅጣጭ የግብር አወቃቀሮች፣ ተጠያቂነት የጎደለው የፖሊስ መምሪያ እና ድህነትን ከስር መሰረቱን አውጥቶ ከመቅረፍ ይልቅ በወንጀል የሚፈርጅ አስተዳደር። እኛ ስለ እሴቶች ብቻ የሚናገር ሳይሆን፣ ግን ያለውን የሚኖር አመራር እንፈልጋለን።

እንደ አንድ የረዥም ጊዜ ተሟጋች፣ የለውጥ ፖሊሲዎች እንዲያልፉ ረድቼአለሁ:- JumpStart Seattle፣ Pay Up Law፣ የተገደቡ የመላኪያ ክፍያዎች፣ ከቤት ውጭ የመመገቢያ ፈቃዶች፣ እና $28.6 ቢሊዮን ዶላር በአገር አቀፍ ደረጃ ላሉ ገለልተኛ ምግብ ቤቶች የፌደራል የመልሶ መቋቋሚያ። እኔ ነገሮች እንዴት እንደሚከናወኑ አውቃለሁ፣ እና እኔ በየእለቱ ለወረዳችን ይህን ለማከናወን ዝግጁ ነኝ።

ከትርፍ በላይ ሰዎችን ማዕከል የሚያደርግ በዋጋ ተመጣጣኝ የመኖሪያ ቤቶች፣ በማህበረሰ-መር መፍትሄዎች ላይ የተመሰረተ የህዝብ ደህንነት፣ እና አነስተኛ የንግድ ሥራዎች እና ሰራተኞች የሚለሙበት የበለፀገ የአካባቢ ኢኮኖሚ ለመስራት ቆርጬያለሁ።

እኛ በጋራ፣ የዋጋ ተመጣጣኝነት ያላት፣ ተጠያቂነት ያላት እና ሁሉንም እንኳን ደህና መጣችሁ የምታሰኝ ከተማ መገንባት እንችላለን። እስኪ ስልጣንን ከትላልቅ ንግዶች/ ኮርፖሬሽኖች ጥቅም እናንሳ እና ሲያትልን ቤታቸው ወደ አደረጉ ሰዎች እናዙር። እኔ እያንዳንዱ ሁሉም ሰው ማን የሆነበት እና ሁሉም የሚበለፅግበት ከተማ ለመፍጠር እንዲረዳ የእርስዎን ድምጽ እጠይቃለሁ።

*እኚህ እጩ በዴሞክራሲ ቫውቸር ፕሮግራም ውስጥ እየተሳተፉ ነው።*



የእጩ ስም፦ ጄሚ ፋክለር (Jamie Fackler)

የምርጫ ዘመቻ ስም፦ ጄሚ ለሲያትል (Jamie for Seattle)

የምርጫ ዘመቻ ድር ጣቢያ፦ jamieforseattle.com

የሚወዳደሩበት ከተማ አስተዳደር ሥልጣን፦ የከተማ ምክር ቤት ወንበር 2

የምርጫ ዘመቻ ስልክ ቁጥር፦ 206-963-3211

ሲያትል ዓለማችን ላይ ካሉት እጅግ የበለጸጉ ከተሞች አንዷ ነች፣ ግን እንደዚያ አይሰማም። ታክስን የሚከለክሉ ቢሊየነሮች አሉን፣ ቤተሰቦች ግን ከመሠረታዊ ነገሮች ውጭ ይሄዳሉ። ይህ የሀብት ቀውስ አይደለም፣ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮች ቀውስ ነው።

ሠርቶ አደሩ የኅብረተሰባችን ክፍል እዚህ ከተማ ውስጥ ቤት ገዝቶ፣ ጥሩ ሕይወት ይኖር የነበረበት ጊዜ ነበር። አሁን ላይ ያለውን አስቸጋሪ አዲስ የኑሮ ሁኔታ መቀበላችን ግድ አይደለም። እያንዳንዱ ሰው ቤት ያለው፣ እያንዳንዱ ልጅ ወደ ትምህርት ቤት የሚሄድበት ደህንነት የሚሰማው፣ እና ማህበረሰባችን በተስፋ የተሞላበት ሲያትል ለመፍጠር እየሮጥኩ ነው።

ከፍተኛ ጥራት ያላቸው የሕዝብ መኖሪያ ቤቶች፣ በህብረት የተገነቡ ቤቶችን እንደ የህዝብ ጥቅም ለማቅረብ ማህበራዊ ቤቶችን እደግፋለሁ። ለዘለቄታው በተመጣጣኝ ዋጋ የመኖሪያ ቤት እድሎችን አሰፋለሁ፣ የተከራይ መብቶችን እጠብቃለሁ እና የመጠለያ አቅምን እገነባለሁ። የእኔ ቢሮ የመድኃኒት እና የአእምሮ ጤና ቀውሶችን ለመፍታት የሚሠሩትን የእንክብካቤ ቡድን (Care Team) እና ድጋፍ ሰጪ ድርጅቶችን ያሰፋል። ግልጽ የተጠያቂነት አሠራሮች ካልተቀመጡ በስተቀር ለፖሊስ መምሪያው አዲስ በጀት እንዲለቀቅ አንስማማም፣ ለተለያዩ ልዩ ልዩ የማኅበረሰብ ደኅንነት ድርጅቶች ድጋፍ እናቀርባለን፣ በከተማይቱም ዳግም የደኅንነት ስሜት እንዲሰፍን እናደርጋለን። እኔ በሞያዬ ፖለቲከኛ አይደለሁም፣ ሆኖም ግን በከተማችን ምክር ቤት ውስጥ መደበኛ ዜጋውን የሚወክል ሰው እንደሚያስፈልግ አምናለሁ።

ድጋፍ ሰጪዎች፦ ኪንግ ካውንቲ ዴሞክራትስ (King County Democrats)፣ 37ኛ ዲስትሪክት ዴሞክራትስ (37th District Democrats)፣ የካውንቲ ምክር ቤት አባል ቴሬሳ ሞስክዊዳ፣ ታሚ ሞራሌስ፣ ሌሪ ጎሴት፣ ኤም.ኤል.ኬ ሌይበር (MLK Labor)፣ ፕሮቴክት17 (PROTEC17)፣ ILWU19፣ ATU587፣ SUP፣ IAM751፣ ኤ.ኤፍ.ቲ ዋሺንግተን (AFT Washington)፣ UAW4121። ድጋፋዎን ባገኝ ትልቅ ክብር ይሰማኛል።

*እኚህ እጩ በዴሞክራሲ ቫውቸር ፕሮግራም ውስጥ እየተሳተፉ ነው።*



የእጩ ስም:- ጄሲ ኤ. ጄምስ (Jesse A. James)

የምርጫ ዘመቻ ስም:- ጄሲ ኤ ጄምስ ለሲያትል

የዘመቻ ድህረ ጣቢያ:- jesseajames.com

የከተማው የምርጫ የስራ መደብ:- የከተማው ምክር ቤት የስራ መደብ 8

የዘመቻ ስልክ ቁጥር:- (206) 657-7062

እንደ አንድ የሺህኛ ምዕተ ዓመት ሙዚቀኛ/ጸሐፊ በሲያትል ውስጥ የመስራት እና የቤት መከራየትን ትግል በቅርበት ስለማውቅ፣ እንደ አንድ የምክር ቤት አባል የኔ ዋና ተቀዳሚ ተግባር የሚሆነው ሲያትልን አስተማማኝ እና ለሁሉም ሰው በተመጣጣኝ ዋጋ መኖር ማድረግ ነው።

በ2022 ውስጥ፣ እኔ ለሕግ አማካሪ ጉባኤ አባልነት የተወዳደርኩት የግብር ማሻሻያ እና የመራቢያ መብቶችን መጠበቅ ማዕከል ባደረገ መድረክ ላይ ነው። እኔ በ2024 አዲሱን ካስኬድ ፓርቲ (Cascade Party) ተቀላቅያለሁ፣ እና በነጻነት የመናገር እና ሁለንተናዊ የጤና አጠባበቅን ወደ መድረክ እንዲጨመር በተሳካ ሁኔታ የተደረገውን ግፊት ተከትሎ የቦርዱ አባል ሆኜ ተመረጥኩ።

እኔ ወደ አካባቢያዊ አስተዳደር ሲመጣ ርዕዮተ ዓለም ከተግባራዊነት እና ከማህበረሰብ ይልቅ የኋላ መቀመጫ መውሰድ አለበት ብዬ አምናለሁ። እውነተኛ ለውጥ የሚመጣው እዚህ ላይ ነው።

የፌዴራል ፖሊሲ ምስቅልቅል ነው፣ እና እኛ በአካባቢ አስተዳደር ውስጥ መረጋጋት እንዲሆን እንፈልጋለን። ሲያትል ባለፉት ሁለት ዓመታት ከተማችን ለንግድ ሥራ ማራኪ ሆና እንድትቆይ ቢደረግም፣ በሕዝብ ደኅንነት እና መኖሪያ ቤት በመስራት ማሻሻል አሳይታለች። ነገር ግን አነስተኛ የንግድ ሥራዎችን እየደገፍን፣ ርህራሄ አድራጊ ማህበራዊ ፕሮግራሞችን በማቅረብ፣ ጣፋጭ በታውን ማግኘት እንችላለን።

እኔ የቀላል ባቡር መስፋፋትን መቀጠል አቅፈዋለሁ። እኔ የስኳር ግብርን ለመሰረዝ አንድ ተሟጋች ነኝ። እነዚህ ፖሊሲዎች ከዓላማዬ ጋር የሚሰሩ፣ ለምክር ቤቱ ተጠያቂነትን እና ሚዛናዊነትን ለማምጣት የታሰቡ፣ እና እኔም ተግባራዊ እንዲሆኑ የተዘጋጀሁ ነኝ!

በKrist Novoselic እና በሌሎችም የተደገፈ።

*ይህ እጩ በዲሞክራሲ ቫውቸር ፕሮግራም ውስጥ እየተሳተፈ አይደለም።*



የእጩ ስም:- ራቻኤል ሳቬጅ (Rachael Savage)

የምርጫ ዘመቻ ስም:- የራቻኤል ሳቬጅ ጓደኞች - የከተማው ምክር ቤት

የዘመቻ ድህረ ጣቢያ:- http://www.savageforseattle.com

የከተማው የምርጫ የስራ መደብ:- የከተማው ምክር ቤት የስራ መደብ 8

የዘመቻ ስልክ ቁጥር:- (206) 657-7062

እንደ አንድ የሲያትል የንግድ ድርጅት ባለቤት ፖለቲከኞች የወንጀል ፍትህ ስርዓታችንን በማፍረስ፣ ወንጀል እንዲቀጥል በማድረግ፣ ሱስ እና ሞት የሚያስከትል የአእምሮ ህመም በመፍቀድ፣ የንግድ ቤቶቻችን እና ውብ መሃል ከተማ ውድመት እና የእያንዳንዱ ዜጋ ደህንነት ስሜት የሚያጠፋ መዘዝ እያየሁ እኔም መኖር ነበረብኝ። እንደ አንድ ነዋሪ እኔም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ከመጣው የቤት ኪራይ ጋር መታገል ነበረብኝ እና ቤት ከመግዛት ዋጋ ውጭ ሆኜ ቤት ከመግዛት እንድቀር አጋጥሞኛል። እንደ አንድ የከተማ ምክር ቤት አባልነቴ፣ የኔ ተልእኮ የደመወዝ ክፍያ የቤት ኪራይ ክፍተቱን የሚዘጋ ተጨባጭ ፖሊሲን በማሳለፍ፣ የፖሊስ መምሪያችንን እንደገና የሚገነባ፣ የራሳችንን የከተማ እስር ቤት የሚያስጠብቅ፣ እስራትን እና የእስር ቅጣት ውሳኔዎችን የሚፈቅድ እና የዕፅ/ መድሃኒት እና የአእምሮ ህመም ወረርሽኙን ለመፍታት የረዥም ጊዜ የነዋሪ መታከሚያ ማዕከላትን በመገንባት እርስዎን ማገልገል ይሆናል።

እኛ የተሻለ መስራት እንችላለን። እያንዳንዱ ማንኛውም ዜጋ በህግ ስር ፍትሃዊ በሆነ መልኩ እንዲስተናገድ እና የሰላም፣ የተረጋጋ፣ የበለጸገ ማህበረሰብ ውስጥ እንዲኖር ተመሳሳይ ምኞት አለው። ደህንነት ንግድ እና ብልጽግናን እንደገና ወደ ከተማችን ያመጣል። ይህንን አንድ ላይ ማድረግ እንችላለን። በእርስዎ ድምጽ መስጠት፣ እኔ ያልተሰማ ድምጽን፣ የጋራ አስተሳሰብ ድምጽን፣ የተባበረ ድምጽን በመወከል ለረጅም ጊዜ ለኛ ሳይሰራ ጋሬጣ ሆኖ የቆየውን ስርዓት በመቃወም እሠራለሁ። የዲሞክራሲ ቫውቸሮች የውጭ ሰዎችን ገንዘብ ለመደገፍ ይረዳሉ። እርስዎ ዛሬ በርስዎ የዲሞክራሲ ቫውቸሮች የእኔን ዘመቻ ይደግፉ።

እኚህ እጩ የዴሞክራሲ ቫውቸር ፕሮግራም ተሳታፊ ናቸው።



የምርጫ እጩ ስም:- ሬይ ኤ. ሮጀርስ (Ray A. Rogers)

የምርጫ ዘመቻ ስም:- ሬይ ኤ. ሮጀርስ (ለሲያትል ከተማ ምክር ቤት፣ የምርጫ ወንበር 8)

የዘመቻ ድር ጣቢያ:- www.RayRogersForSeattle.com

የምርጫ ወንበር:- 8

የዘመቻ ስልክ ቁጥር:- 206-641-0859

እኔ ሁኔታውን በመኖሬ ምክንያት መንግስት ሲወድቅ ምን እንደሚሆን አውቃለሁ። እኔ ያደግሁት ደቡብ ምስራቅ ሲያትል ውስጥ እኔን ጨምሮ፣ ብዙ ልጆች ወደ ሁከትና ሱስ ውስጥ በተሳቡበት ወቅት ነው። እኔ የቤት እጦት፣ የዕፅ ሱሰኝነትን እና እስር ቤት ከመዳረግ ጋር ለዓመታት እየተዋጋሁ አሳልፌያለሁ። ሕይወቴ በዚያ ሊያበቃ ይችል ነበር። ነገር ግን አልሆነም፤ ምክንያቱም ሌላ ማንም ሊያደርገው ባልፈለገበት ጊዜ የማህበረሰቡ መሪ ጊዜ ወስዶ በኔ ላይ እምነት በማድረጉ ነው። እኔ ሕይወቴን ዙሪያውን አዞርኩት። እና ላለፉት 20 አመታት፣ እኔ ሌሎችም ተመሳሳይ ነገር እንዲያደርጉ ለመርዳት በመስራት ላይ ነበርሁ።

አሁን እኔ ለሲያትል ከተማ ምክር ቤት እጩ ሆኜ እየተወዳደርኩ ነኝ ምክንያቱም ከተማችን መንታ መንገድ ላይ ነች። እኔ ወንጀልን እና ሱስን በመዋጋት መሬት ላይ ያለ እውነተኛ ልምድ አለኝ። ለሱስ፣ ለአመጽ እና ለቤት እጦት የተጋለጡ ሰዎችን የሚደግፍ፣ የፍቅር ማዳረስ አውድ (Circle of Love Outreach) የተባለውን ሥር ነቀል ፕሮግራም መስርቻለሁ።

አንዳንድ በምክር ቤቱ ያሉ ያን ያክል ጉዳት ያደረሱብንን ወደማይሰራ ብልሹ፣ መከፋፈል እና ክህደት ሊመልሱን ይፈልጋሉ። ይህ እንዲሆን አይፍቀዱ። እኔ ሰዎች በርህራሄ እና በጥድፊያ፣ ከድንኳኖች ወጥተው ወደ መኖሪያ ቤት እንዲዛወሩ እሰራለሁ። እኔ በወጣቶች ፕሮግራሞች፣ በአመፅ መከላከል፣ በአእምሮ ጤና ድጋፍ እና በእውነተኛ ኢኮኖሚያዊ ዕድል ላይ መዋዕለ ንዋይ አደርጋለሁ—ምክንያቱም ያን እኛ ሳናደርግ ቀርተን የሚሆነውን አይቻለሁና። እና እኔ ማህበረሰቦቻችንን ንቃት የሚያስተጋባ ሆነው እንዲቆዩ ለሚያደርጉት አነስተኛ ንግዶች እቆማለሁ።

ይህ እጩ በዲሞክራሲ ቫውቸር ፕሮግራም ውስጥ እየተሳተፈ አይደለም።



የእጩ ስም፦ አሌክሲስ ሪንክ (Alexis Rinck)

የምርጫ ዘመቻ ስም፦ አሌክሲስ ለሲያትል (Alexis for Seattle)

የምርጫ ዘመቻ ድር-ጣቢያ፦

www.alexisforseattle.com/

የሚወዳደሩበት ከተማ አስተዳደር ሥልጣን፦ የከተማ ምክር ቤት ወንበር 8

የምርጫ ዘመቻ ስልክ ቁጥር፦ 206-705-9305

የእኔ ጽሕፈት ቤት በአጭር ጊዜ ውስጥ ማሳካት በቻላቸው ነገሮች ኩራት ይሰማኛል፦

- ትላልቅ ኮርፖሬሽኖች ላይ በሚጣል ግብር ተመጣጣኝ ዋጋ ያላቸው መኖሪያ ቤቶች ግንባታን በገንዘብ ለመደገፍ 63% ድምጽ አግኝቶ በዚህ ዓመት የጸደቀውን Prop 1A መደገፍ።

- በአካባቢው የሚገኙ ባለሙያዎች እና መሪዎችን የሚያሰባስብ ልዩ ኮሚቴ በመምራት ከተማችንን ከፌደራል ፖሊሲ ለውጦች ለመከላከል የሚደረገውን ትግል በግንባር ቀደምነት ማከናወን።

- ተራማጅ የግብር ፖሊሲን በመደገፍ ተመጣጣኝ ዋጋ ያላቸው መኖሪያ ቤቶች፣ የምግብ ተደራሽነት እና ሌሎች አገልግሎቶችን ከበጀት ቅነሳዎች እየጠበቅን አነስተኛ ንግድ ሥራዎች ላይ ያለውን ጫና መቀነስ።

ተከራይ፣ የአውቶቡስ ተጠቃሚ እና የቀድሞ አስተናጋጅ እንደመሆኔ መጠን በድጋሚ ለመመረጥ ለመወዳደር እና ይህን ሥራ ለመቀጠል ጉጉት ይሰማኛል። ከMLK Labor፣ The Stranger፣ One America Votes፣ The Urbanist፣ ዲሞክራቲክ ቡድኖች፣ የSeattle ከተማ አስተዳደር የምክር ቤት አባል Dan Strauss፣ በእያንዳንዱ የSeattle የሕግ አውጪ ዲስትሪክት የሚገኙ ሕግ አውጪዎች፣ Seattle የሚገኘው እያንዳንዱ የKing County የምክር ቤት አባል እና ሌሎች ተጨማሪ አካላት ድጋፍ በማግኘቴ ኩራት ይሰማኛል። የእርስዎንም ድጋፍ እንደማገኝ ተስፋ አደርጋለሁ!

እባክዎ የበለጠ ለማወቅ የዲሞክራሲ ቫውቸሮችዎን ይስጡ እና AlexisForSeattle.comን ይጎብኙ።

*እኚህ እጩ በዴሞክራሲ ቫውቸር ፕሮግራም ውስጥ እየተሳተፉ ነው።*



**የእጩ ስም፡-** Dionne Foster

**የምርጫ ዘመቻ ስም፡-** Dionne ለሲያትል

**የምርጫ ዘመቻ ድር ጣቢያ፡-** dionnefoster.com

**የሚወዳደሩበት ከተማ አስተዳደር ሥልጣን፡-** የሲያትል የከተማ ምክር ቤት ወንበር #9

**የምርጫ ዘመቻ ስልክ ቁጥር፡-** 206-651-5493

*ደኅንነታቸው የተጠበቁ ጎዳናዎች፣ ተመጣጣኝ ዋጋ ያላቸው መኖሪያ ቤቶች እና መብቶቻችንን የሚጠብቁ እና ድምጻችንን የሚያከብሩ የሲያትል መሪዎችን ማግኘት ይገባናል።*

Dionne Foster የፖሊሲ ኤክስፐርት፣ የማህበረሰብ መሪ፣ የሰለጠነች የማህበራዊ ጉዳይ ሰራተኛ እና ማህበረሰቦቻችንን የበለጠ ደህንነታቸው የተጠበቀ፣ የበለጠ ዘላቂ እና የበለጠ ፍትሃዊ በማድረግ ከአስር አመታት በላይ ያሳለፈች እናት ነች።ይህንን አዎንታዊ የአመራር ታሪካቸውን መሠረት በማድረግ ለከተማ ምክር ቤት እየተወዳደሩ ሲሆን፣ ምክር ቤቱ ከግል አጀንዳዎች ይልቅ ቅድሚያ የሚሰጣቸው የጋራ ጉዳዮች እና አስቸኳይ ፍላጎቶች ላይ ዳግም እንዲያተኩር ያደርጋሉ።

በWA Progress Alliance ባላቸው የሥራ አስፈጻሚ ዳይሬክተርነት ሚና ውስጥ ባለሃብቶች ላይ ፍትሐዊ የሆነ ግብር መጣሉን በማረጋገጥ እና የዋጋ ተመጣጣኝነት እና የገንዘብ ድጋፍ ፍላጎቶችን በመፍታት ስቴት አቀፍ የካፒታል ትርፍ ግብር ላይ ባሳዩት አመራር በልጆች እንክብካቤ፣ በቅድመ መደበኛ ትምህርት እና በትምህርት ቤት ግንባታ ዙሪያ ታሪካዊ ኢንቬስትመንቶች እንዲጸድቁ እና ተጠብቀው እንዲቆዩ ማድረግ ችለዋል።

Dionne በሲያትል ከተማ አስተዳደር ከፍተኛ የፖሊሲ አማካሪ እንደመሆናቸው መጠን የሕዝብ ደኅንነትን ለማሻሻል፣ ለወጣቶች ዕድሎችን ለመፍጠር እና የአየር ንብረት ግቦችን ለማሳካት የባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ አስተዳድረዋል። በሲያትል ፋውንዴሽን አዳዲስ የመኖሪያ ቤት ስትራቴጂዎችን በመፍጠር እና ጠንካራ ኢኮኖሚን በማዳበር ላይ የሚገኙ ድርጅቶች ላይ ኢንቬስት አድርገዋል።

ከእርስዎ ድጋፍ ጋር, Dionne ሀገራዊ ችግሮችን ለመፍታት ሲያትልን አንድ ላይ ለማምጣት ትረዳለች እና በከተማችን ውስጥ ሁሉም ሰው ደህንነት እንዲሰማው፣ አቀባበል እንዲደረግለት እና እንዲደገፍ ለመርዳት የአካባቢ እድገትን ትመራለች።። Dionne በዚህ ውድድር ውስጥ በMLK የሠራተኛ ምክር ቤት የሚደገፉት ብቸኛው እጩ ናቸው።

*እኚህ እጩ በዴሞክራሲ ቫውቸር ፕሮግራም ውስጥ እየተሳተፉ ነው።*



**የእጩ ስም:-** ሳራ ኔልሰን

**የዘመቻ ስም**:- ሳራ ኔልሰን ለከተማ ምክር ቤት

**የዘመቻ ድር ጣቢያ:-** SaraForCityCouncil.com

**የስራ መደቡ**:- የሲያትል ከተማ ኮሚቴ አቀማመጥ 9 በአጠቃላይ

**የዘመቻ ስልክ ቁጥር :-** 206-821-6140

እኔ ሳራ ኔልሰን ነኝ፣ የከተማዎ አጠቃላይ የምክር ቤት አባል።

ከአራት ዓመታት በፊት፣ ሲያትል ተጣብቆ ነበር - እድገት ያሉ ወንጀሎች፣ በመናፈሻችን ውስጥ ሰፈሮች እና መሻሻል ከማሳየት ይልቅ መግለጫዎችን ለመስጠት የበለጠ ፍላጎት ያለው ምክር ቤት ፊት ለፊት። ያንን ለመለወጥ ሮጥኩ።

ዛሬ፣ በመጨረሻ አቅጣጫ እየቀየርን ነው። ሲያትል ከ2019 ጀምሮ ለመጀመሪያ ጊዜ ከምናጣው በላይ የፖሊስ መኮንኖችን እየቀጠረ ነው። ከ Evergreen Treatment አገልግሎቶች ጋር ያለንን አጋርነት በማስፋት የፌንታኒል ወረርሽኙን ፊት ለፊት እየፈታን ሲሆን ይህም የሞባይል መድሃኒትን እና ከኦፒዮይድ አጠቃቀም ዲስኦርደር ጋር ለሚታገሉ ሰዎች ድጋፍ ያደርጋል። እና የሰፈር ንግዶች መሰባበር ሲያጋጥማቸው ወጪዎቻቸውን መልሰው እንዲያገኙ እንዲረዳቸው የመድብር የፊት ለፊት ጥገና ፈንድ ፈጥረናል።

እኔ የነበረኝን የመልሶ ማግኛ ዕድል ሁሉም ሰው ይገባዋል። ለዚያም ነው በከተማችን ውስጥ የአደጋ ጊዜ ምላሽን እያሻሻልኩ፣ ነፃ፣ በፍላጎት ህክምና በመስጠት ላይ ያተኮርኩት።

ማለቂያ የሌለው ክርክር ሳይሆን ውጤት ለማምጣት አምናለሁ። ያ ትናንሽ ንግዶች እንዲበለፅጉ መርዳትም ሆነ ከተማችንን በጣም ንቁ የሚያደርጉ ማህበረሰብ አቀፍ ተቋማትን መደገፍ።

የሚያጋጥሙን ፈተናዎች ውስብስብ ናቸው ነገርግን አንድ ላይ ሆነን እውነተኛ እድገት ማድረግ እንችላለን። ይህንን ስራ ለመቀጠል ድጋፍዎን በማግኘቴ ኩራት ይሰማኛል።

*ይህ እጩ በዲሞክራሲ ቫውቸር ፕሮግራም ውስጥ እየተሳተፈ አይደለም።*